የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት

የንግድ ምልክት ወኪሎች የብቃት ምዘና፣ ምዝገባ እና አሰራር መመሪያ ቁጥር 644/2013

መጋቢት 2011 ዓ.ም

መግቢያ

የንግድ ምልክት ወኪልነት አገልግሎት ብቃት ላይ የተመሰረተ በታማኝነትና በታታሪነት የሚሰራ ስራ በመሆኑ፣ የንግድ ምልክት ወኪሎች ብቃት ደረጃ ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር የተመጣጠነ እንዲሆንና የተገልጋዩን ፍላጎት በሚያረካ የእውቀት ብቃት ላይ መመስረት ስላለበት የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 273/2005 አንቀፅ 51 ለፅ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን የንግድ ምልክት ወኪሎች የብቃት የምዘና፣ ምዝገባና አሰራር ሥርዓት መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ "የንግድ ምልክት ወኪሎች የብቃት ምዘና፣ ምዝገባና አሰራር መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የማያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

   1) "አዋጅ" ማለት የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 ነው፣
   2) "ደንብ" ማለት የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 273/2005 ነው፣
   3) በአዋጁና በደንቡ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች በዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፣
   4) "ዋና ዳይሬክተር" ማለት የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር ማለት ነው፣
   5) "የሥራ ክፍል" ማለት በጽ/ቤቱ የሚገኙ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች ማለት ነው፣
   6) "ወኪል ማለት" በደንቡ 51 (1) መሰረት ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ ጋር በተያያዘ ንግድ ምልክት ባለቤቶችን ለመወከል የሚያስችል በጽ/ቤቱ የሚሰጠውን የብቃት መመዘኛ ወስዶ የተመዘገበ የተፈጥሮ ሰው ማለት ነው፡፡
   7) "የወኪሉ ረዳት ማለት" በወኪሉ ስር በመሆን በወኪሉ የተዘጋጁ ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ ጋር የተያያዙ ማመልከቻዎችና የሚያቀርብ ሰነዶችን ከ/ጽቤቱ ፈርሞ የሚረከብ፣ ክፍያዎችን የሚፈጽም እና ሌሎች መሰል ስራዎችን ለመከወን በወኪሉ ውክልና የተሰጠው ግለሰብ ማለት ነው፡፡

ኤርሚያስ የማነብርሃን
ዋና ዳይሬክተር

8) "መካከለኛ የትምህርት ደረጃ" ማለት በማንኛውም የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ማለት ነው፡፡

ክፍል ሁለት

ስለ ፈቃድ አሰጣጥ እና ስለ የንግድ ምልክት ወኪሎች ምዝገባ

3). ስለማመልከቻ አቀራረብ

1) ለወኪልነት ምዝገባ የሚቀርብ ማመልከቻ በጽ/ቤቱ በተዘጋጀ ቅጽ ተሞልቶ ይቀርባል፡፡

2) አመልካቹ ከማመልከቻው ጋር የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይኖርበታል፡-

ሀ) የትምህርት ማስረጃ ዋናውን ከአንድ ኮፒ ጋር፣

ለ) ከንግድ ምልክት ጋር የተያያዘ አገልግሎት የሰጠ ከሆነ ይህንን የሚያሳይ ህጋዊ ማስረጃ ዋናውን ከአንድ ኮፒ ጋር፤

ሐ) የጥብቅና ፈቃድ ያለው አመልካች የታደሰ የጥብቅና ፈቃዱን ዋናውን ከአንድ ኮፒ ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

መ) ለምዝገባ የተከፈለበትን ደረሰኝ አንድ ኮፒ

ሠ) የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ አግባብ ካለው የመንግስት አካል የተሰጠው የሥራ ፈቃድ /work permit/ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ረ) ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፍ ይዞ መቅረብ አለበት፡፡ ጽ/ቤቱም ለፈተና እንዲቀርቡ የሚያገለግል መታወቂያ /Admission Card/ መስጠት ይኖርበታል፡፡

4). የወኪሎች ምዝገባን ስለማካሄድ፣

1) በደንቡ አንቀጽ 51 በተደነገገው መሰረት የንግድ ምልክት ወኪሎች ምዝገባ ይካሄዳል፡፡ በዚህም መሰረት፡-

ሀ) የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ያለው ጠበቃ

ለ) አግባብ ባለው የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ መካከለኛ ትምህርት ደረጃ ያለውና ከንግድ ምልክት ስራ ጋር በተያያዘ ከሶስት ዓመት ያላነሰ ልምድ ያለው እንዲሁም በሕግ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ከሆነ ቢያንስ ሁለት አመት የሥራ ልምድ ያለው በጽ/ቤቱ የሚሰጠውን የብቃት ምዘና ለመውሰድ ማመልከት ይችላል፡፡

ሐ. የሥራ ልምድ የሚያቀርቡ አመልካቾች ከሰሩበት ተቋም ምንም አይነት የዲስፕሊን ግድፈት የሌለባቸው መሆኑን ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው፡፡

መ. የመንግስት ሠራተኛ የሆነ ማንኛውም ሰው ለንግድ ምልክት ወኪልነት መመዝገብ አይችልም፡፡

ሠ. የወኪል ምዝገባ አመልከቾች ጽ/ቤቱ ባዘጋጀው ቅጽ መረጃቸውን መሙላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

2.) ለወኪልነት ብቃት ምዘና ተፈታኙ ለምዘና ሲቀርብ የቀበሌ መታወቂያ፣ ወይም ፖስፖርት፣ በጽ/ቤቱ የተሰጠውን የማመልከቻ መታወቂያ /Admission card/ አሟልቶ መቅረብ እና የጽ/ቤቱን የፈተና ሥነ ሥርዓት ማክበር ይኖርበታል፡፡

3.) በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ ስራን በወኪልነት ለማከናወን የሚፈልግ አመልካች ለስራው ብቁ የሆነና በጽ/ቤቱ የተመዘገበ መሆን አለበት፤

4.) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሰረት የብቃት መመዘኛ ወስዶ ያለፈ አመልካች ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም የወኪልነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

5.) የምዝገባ ምስክር ወረቀቱም፡-

ሀ) የወኪሉን ሙሉ ስም ዕድሜና ዜግነት

ለ) መደበኛ መኖሪያና የስራ አድራሻ

ሐ) ወኪሉ የሚሰማራበት የስራ መስክ

መ) ምዝገባ ቀን

ሠ) የፈቃድ ሰጪው ስምና አድራሻ እና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎችን አካቶ መያዝ አለበት፤

ረ. የወኪሉ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ፎርማት እንደ መታወቂያ ሆኖ ኮፒው ከፍይሉ ጋር ቀሪ መሆን አለበት፡፡

6. የወኪሎች ምዝገባ ማመልከቻ የሚቀርበው ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

7. አመልካቾች ለፈተና እንዲቀርቡ የፈተና ጊዜው በጽ/ቤቱ ማስታዎቂያ ሰሌዳ ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ዘዴ ይገለጻል፡፡

8. የወኪልነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት እና የምዝገባ ምስክር ወረቀት እድሳት በጽ/ቤቱ በኩል ይፈፀማል፡፡

ኦርማያስ የ... ዋና ዳይሬክተር

9. የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት የእያንዳንዱን ወኪል የስራ እንቅስቃሴ የተመለከተ መረጃ ይይዛል፡፡
10. ፈተና ወስዶ ያላለፈ አመልካች በቀጣይ ፈተና የመውሰድ መብቱ የተጠበቀ ነው፤
11. ማንኛውም አመልካች ቀደም ሲል የንግድ ምልክት ወኪል ሆኖ ሲያገለግል ከቆየና የብቃት ፈተናንውን ወስዶ ማለፍ ካልቻለ የጀመራቸውን ከንግድ ምልክት ምዝገባ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ሊያጠናቅቅ ይችላል፡፡
12. በጽ/ቤቱ ውስጥ በንግድ ምልክት ምርመራ ባለሙያነት ተቀጥሮ ሲያገለግል የነበረ ባለሙያ በተለያየ ምክንያት ከስራው ቢሰናበት ከምርመራ ስራው ከተለየ ጊዜ ጀምሮ አንድ ዓመት ሳይሞላው በንግድ ምልክት ወኪልነት ሊሰማራ አይችልም፡፡
13. የጽ/ቤቱ ሰራተኛ የአእምሯዊ ንብረት ትሪቡናል ውስጥ ሲሰራ የመረመራቸውን የንግድ ምልክት ጉዳዮች በድጋሚ በወኪልነት ሊይዝ አይችልም፡፡
14. የብቃት መመዘኛውን ወስዶ ያለፈና በጽቤቱ የተመዘገበ ዓመልካች ስራ ከመጀመሩ በፊት በጽ/ቤቱ የህግ ጉዳዮች አገልግሎት ሃላፊ ፊት በመቅረብ የሚከተለውን ቃለ መሃላ ይፈጽማል፡፡ እኔ-------------------ዛሬ-------------------ቀን-------- ዓ.ም በጽ/ቤቱ የንግድ ምልክት ወኪልነት ስራ ፈቃድ ስቀበል በሙያዬ በቅንነትና በታማኝነት በመስራት የምወክላቸውን የደንበኞችን ጥቅም ህግ በሚፈቅደው መጠን ላስከብር፤ ከጽቤቱ ባለሙያዎችና ከሙያ ባልደረቦቼ ጋር በመግባባት ልሰራና ለህግ መከበር አጋዥ ለመሆን ቃል እገባለሁ፡፡

5) *የንግድ ምልክት ወኪሎች ብቃት ምዘና ኮሚቴ ስለማቋቋም*

1) ጽ/ቤቱ የንግድ ምልክት ወኪሎች ምዘና ሥርዓት ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል
2) የጽ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር አግባብነት ካላቸው የስራ ክፍሎች የተውጣጣ 5 ዓባላት ያሉት የንግድ ምልክት ወኪሎች ብቃት ምዘና ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡
3) የእያንዳንዱ የኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፡፡ ነገር ግን በዋና ዳይሬክተር ሲታመንበት ለተጨማሪ አንድ ዓመት ሊራዘም ይችላል፡፡
4) የጽ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ከኮሚቴው አባላት መካከል ፀሀፊና ሰብሳቢ ይሰይማል፡፡

6) *የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር*

ኮሚቴው፤

1) በዚህ መመሪያ መሰረት የምዘና ስራን ያከናውናል፤

2) ስለ ፈተናው አሰጣጥ ሁኔታ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡
3) የምዘና ወረቀቶችን ያርማል፤ የምዘናውን ውጤት ለዋና ዳይሬክተሩ አቅርቦ ሲጸድቅ ውጤቱን ይፋ ያደርጋል፡፡
4) የኮሚቴው አባላት ሚስጢር የመጠበቅ ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡
5) ከኮሚቴው አባላት መካከል ግዴታቸውን ያልተወጡ ካሉ በማንኛውም ጊዜ ኮሚቴው ተወያይቶለዋና ዳይሬክተሩ በማቅረብ ከአባልነታቸው ሊያስነሳ ይችላል፡፡
6) ወኪሎች ለዋና ዳይሬክተሩ የሚያቀርቡትን የውጤት ቅሬታ የጽ/ቤቱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ገምግሞ ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባል፡፡

7) *የምዘና ሥርዓቱ ይዘት*

1) የምዘና ሥርዓቱ 100% የጽሁፍ ነው፡፡ 50+1% የማለፊያ ነጥብ ሆኖ ይሆናል፡፡
2) ፈተናው በእንግሊዘኛ ቋንቋ ይሰጣል፡፡
3) የጽሁፍ ምዘናው ይዘት በኮሚቴው የሚወሰን ሆኖ የሚውጣጣውም ከንግድ ምልክት መሰረተ ሃሳቦችና እና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ሕጎች ይሆናል፡፡

8) *የኮሚቴው ስብሰባ*

1) ኮሚቴው እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡
2) ከኮሚቴው አባላት ሶስትና ከዚያ በላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
3) የኮሚቴው ውሳኔዎች በስብሰባው በተገኙ አባላት በድምጽ ብልጫ ይወሰናል፤ ሆኖም እኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡
4) ዋና ዳይሬክተሩ በኮሚቴው የቀረበውን ሀሳብ ሊያጸናው፣ ሊያሻሽለውና ሊሽረው ይችላል፡፡

9) *የወኪሎች መብት*

በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ስለወኪሎች መብት የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በጽ/ቤቱ ተመዝግበው የሚገኙ ወኪሎች የሚከተሉት መብቶች ይኖራቸዋል ፡

1) በምዘና ውጤት ቅሬታ ያለው ወኪል ውጤቱ በተገለጸለት 15 ቀን ውስጥ ቅሬታውን ለዋና ዳይሬክተሩ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2) በጽ/ቤቱ የሚሰጠውን የብቃት ምዘና ያለፈ ወኪል ከጽ/ቤቱ የብቁነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በደንቡ አንቀጽ 52 (1) እና (2) መሠረት ሰርተፊኬት የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

ዋና ዳይሬክተር

3) በጽ/ቤቱ የተመዘገበ ለመሆኑ በጽ/ቤቱ ድረ-ገጽ ማንነቱ እንዲገለጽለት የመጠየቅ መብት ይኖረዋል፡፡

4) ወኪሉን ወክሎ የተለያዩ ጉዳዮችን የሚያስፈጽም የወኪሉ ረዳት ሆኖ የሚሰራ ሰው የመወከል፣ መብት ይኖራቸዋል።

10) *የወኪሎች ግዴታ*

በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ስለወኪሎች ግዴታ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በጽ/ቤቱ ተመዝግበው የሚገኙ ወኪሎች የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖርባቸዋል ፡

1) የጽ/ቤቱን አሠራሮችና መመሪያዎች የማክበር፣
2) ከጽ/ቤቱ ሥራዎች ጋር በተያያዘ አገልግሎት የሚሰጣቸውን ባለጉዳዮች በሥነ-ምግባርና በቅንነት የማገልገል፣
3) ከጽ/ቤቱ ሥራዎች ጋር በተገናኘ ለደንበኞቻቸው ትክክለኛ መረጃ የመስጠት፣
4) ሌሎች በሃገሪቱ ስለወኪሎች የተደነገጉ ህጎችንና አሰራሮችን የማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡
5) ወኪሉ የምዝና ፈቃድ ማመልከቻ ሲያቀርብ፣ ምስክር ወረቀት ሲሰጠው እና ሲያድስ ለአገልግሎቱ አስፈላጊውን ክፍያ መክፈል ይኖርበታል፡፡

11) *ምዝገባን ስለመሰረዝ፣ ምትክ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት እና ፈቃድ ስለማስመለስ*

1) ምዝገባው የተካሄደው በማታለል ወይም የሀሰት ማስረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ ከሆነ፣
2) በደንቡ አንቀጽ 53 መሰረት የንግድ ምልክት ወኪልነት ምዝገባን ያላሳደሰ ከሆነ፣
3) በወኪሉ ጥያቄ መሰረት ምዝገባውን የተወው ከሆነ የወኪሉ ምዝገባ ከመዝገብ ይሰረዛል፡፡
4) አንድ ወኪል ጽ/ቤቱንም ሆነ ደንበኛውን ለማጭበርበር ወይም ህገወጥ ስራ ሲሰራ የተገኘ እንደሆነ ወይም ከደንበኛው ጋር የገባው ግዴታ ሳይፈጽም ሲቀር አለዛም ደንበኛው በወኪሉ ላይ የሚያነሳውን ቅሬታ በመመርመር በተጨባጭ ማስረጃ ሲረጋገጥ ጽ/ቤቱ የሰጠውን ፈቃድ ሊሰርዝ ወይም ሊያግድ ይችላል።
5) በህገ ወጥ ድርጊት ፈቃዱ የታገደ ወይም የተሰረዘ የንግድ ምልክት ወኪሉ በፈጸመው ጥፋት የተጣለበት የእግድ ጊዜ ሲያበቃ እግዱ የሚነሳለት ወይም እንደገና ፈተናውን መውሰድ የሚችል ይሆናል።

ኤርሚያስ ... ዋና ዳይሬክተር

6) የምዝገባ የምስክር ወረቀት ጽ/ቤቱ ከሰጠ በኃላ ቢጠፋ ወይም ቢሰረቅ ምትክ ለመስጠት አግባብነት ካለው አካል አስመስክሮ መረጃ ማምጣት አለበት።

7) የወኪል ምዝና ፈተናውን ማለፋ ይፋ ከተደረገ ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የምስክር ወረቀቱን ካልወሰደ ምዝገባውን እንደተወው ይቆጠራል።

12.. *የወኪሎች የዲስፕሊን ኮሚቴ ስለማቋቋም/ ተጨማሪ ስራዎች በኮሚቴው የሚካተቱ ይሆናል/*

12.1.የንግድ ምልክት ወኪሎች የዲስፕሊን ኮሚቴ ይቋቋማል። ተጠሪነቱም ለዋና ዳይሬክተር ይሆናል።

12.2.የጽ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር አግባብነት ካላቸው የስራ ክፍሎች የተውጣጣ 5 አባላት ያሉት የንግድ ምልክት ወኪሎች ዲስፕሊን ኮሚቴ ያቋቁማል።

12.3 የኮሚቴው የሥራ ዘመን 2 ዓመት ሲሆን ሰብሳቢ እና ፀሀፊ በዋና ዳይሬክተር ይሰየማል።

13. *ስልጣንና ተግባር*

13.1 በመመሪያው ላይ የተቀመጠውን በመጣስ በወኪሉ ላይ ክስ ሲቀርብ ተቀብሎ ያጣራል ይመረምራል ፡፡

13.2 በወኪሉ ላይ የቀረበውን ክስ ለማየት የሚያበቃ ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ ወኪሉ መልሱን በ30 ቀን ውስጥ እንዲያቀርብ ክሱን ይልካል፤

13.3 በወኪሉ በኩል የተሰጠውን መልስና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የውሣኔ ሀሳብ ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባል፡፡

ክፍል ሶስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14. *የምዘና ሥርዓት ጊዜ*

በጽ/ቤቱ የሚሰጠው ምዘና እንደ አስፈላጊነቱ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰጣል፡፡

15. *የምዘና የሚስጥር ቁጥር፤*

የወኪሎች የምዘና የሚስጥር ቁጥር በዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት በኩል ለወኪሎች ይሰጣል፡፡

ኤርሚያስ የ...
ዋና ዳይሬክተ...

16. *የመሸጋገሪያ ድንጋጌ*

1) የብቃት ምዘና እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ በጽ/ቤቱ ተመዝግበው የነበሩ የንግድ ምልክት ወኪሎች በሥራቸው እንዲቀጥሉ የሚደረግ ሲሆን ጽ/ቤቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚሰጠውን ምዘና ዝግጅቱን እንዳጠናቀቀ በማናቸውም ጊዜ የብቃት ምዘናውን ሊሰጥ ይችላል፡፡

2) በዚህ መመሪያ መሰረት የወኪሎች ምዘናና መረጣ ይፋ ከመሆኑ በፊት የገቡ እና በመታየት ላይ ያሉ መዝገቦችን በውክልና የሚያንቀሳቅሱ ወኪሎች የገቡት መዝገቦች (ጉዳዮች) የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥባቸው ድረስ በዚህ መመሪያ አይተዳደሩም (አይሸፈኑም)፡፡

3) በምዝገባ ወቅት በዓለም አቀፉ የአዕምሯዊ ንብረት ደርጅት የሚሰጠውን አጠቃላይ የአእምሯዊ ንብረት የርቀት ትምህርት መውሰድ ያልቻለ ወኪል ለዕድሳት ጥያቄ በሚመጣበት ወቅት የርቀት ትምህርቱን በማጠናቀቅ ሰርቲፊኬቱን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይህን የርቀት ትምህርት ፈተና ለመስጠት ጽ/ቤቱ ከአለም አእምሯዊ ንብረት ጋር በመተባበር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

17. *መመሪያውን ስለማሻሻል*

በጽ/ቤቱ የማኔጅመንት ዓባላት አብላጫ ድምጽ ሲታመንበት ይህ መመሪያ ሊሻሻል ይችላል፡፡

18. *መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ*

ይህ መመሪያ በጽ/ቤቱ ማኔጅመንት አባላት አብላጫ ድምጽ ከፀደቀበት ከዛሬ መጋቢት....ቀን2011 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

መጋቢት.....ቀን 2011 ዓ.ም

ኤርሚያስ የማነብርሃን

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር

አዲስ አበባ